# በኬንያ ከ4 ሚሊየን ብር በላይ የቦንድ ግዥ ተከናወነ

በናይሮቢ እና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ለኅዳሴ ግድብ 4.375 ሚሊየን ብር የቦንድ ግዥ አከናወኑ።

ኢትዮጵያውያኑ ኅዳር 30 ቀን 2004 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ባካሄዱት የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት 250 ሺህ ዶላር ወይንም 4,375,000 ብር (አራት ሚሊዮን ሶሶት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር) አሰባስበዋል። ቦንዱን ከገዙት ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተጨማሪ ኤርትራዊያንና የሩዋንዳ ዜጐች ይገኙበታል።

በኬንያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሽምሱዲን አህመድ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር ታላቁ የኅዳሴ ግድብ በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ይገንባ እንጂ ቀሪ ሀብትነቱ፣ ኩራቱና ጥቅሙ ለቀጣዩ ትውልድ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአባይን ወንዝ እንዳትጠቀም በውጭ ኃይሎች ከፍተኛ ተጽእኖዎች ይደረግ እንደነበር ያስታወሱት አምባሳደር ሽምሱዲን ይህ ትውልድ በአባይ ላይ እየተገነባ ያለውን ግድብ እውን ለማድረግ ታሪካዊ ዕድል እንደገጠመውም አስረድተዋል።

በግድቡ ግንባታ ሂደት ተሳትፎ ከኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የአባይ ተፋሰስ አገሮች መሳተፋቸውን አምባሳደሩ አድንቀዋል። ይህም የሆነው በግድቡ ግንባታ ተሳትፈው የጥቅሙ ተካፋይ መሆናቸው ስለማይቀርና የባለቤትነት መንፈስ በክፍለ አህጉሩ ዜጐች ቢዳብር ይበጃል ከሚል መንፈስ በመነጨ እንደሆነም አስረድተዋል።

በዕለቱ ዝግጅት ላይ በናይሮቢ የተ.መ.ድ. ጽ/ቤት ኃላፊ አምባሳደር ሣህለወርቅ ዘውዴ በክብር እንግድነት ተገኝተው በቦንድ ግዢ የተሳተፉ ሲሆን፣ እንዲሁም የቀድሞ አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ አባይን ኢትዮጵያ  መጠቀም እንድትችል ከልጅነት ጀምሮ ሲጠብቁ እንደነበር ጠቁመው አሁን የኅዳሴ ግድብን ለመገንባት ሕዝቡ እየተንቀሳቀ በመሆኑ መደሰታቸውን ገልጸዋል። ይህን ግድብ እውን ለማድረግ ከገንዘብ በተጨማሪ ለረዥም ጊዜ የሚዘልቅ የመንፈስ ዝግጁነት ያስፈልጋል ብለዋል።

በናይሮቢ የደብረመድሃኒት የመድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አባ መልአከሰላም አባ ቆምስ አባ ሃብተማሪያም ወ/ጊዮርጊስ በበኩላቸው ቤተክርስቲያኗ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የተሳካ እንዲሆን በፀሎት በገንዘብና ምዕመናንን በማስተባበር ወደፊትም እንደምትሰራ አስታውቀዋል።

ሩዋንዳዊው የዓለም አብያተክርስቲያናት ኮንፈረንስ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር አንድሬ ካራማጋ በበኩላቸው ቦንዱን ለመግዛት በመታደላቸው ደስታቸውን በመግለጽ ኢትዮጵያ ጥንትም ቢሆን የአፍሪካ ኩራት እንደሆነች ተናግረዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ድርጅት ባለሙያ የሆኑት አቶ ሄኖክ ኡቻላ በበኩላቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው የሚካሄደውን የልማት ሥራ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበው የጋምቤላ ብሔር ተወላጅ የሆኑና በኬንያና በሌሎች አገሮች ነዋሪ የሆኑትን የዲያስፖራ አባላት አስተባብረው ግድቡን ከግቡ ለማድረስ እንደሚንቀሳቀሱ አስታውቀዋል፡፡

በዚሁ ስነ ስርዓት ላይ በኢትዮጵያውያን አርቲስቶች የብሔር ብሔረሰቦች የባህላዊ ሙዚቃ ዝግጅት እና ግጥም ቀርቧል፡፡